EthioLion

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ የወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢሕአፓ ወክንድ)

Ethiopian People's Revolutionary Party Youth League (EPRP YL)

መጋቢት 19 2004 ዓም

# የኢትዮጵያን መምህራን ትግል በሙሉ ልብ እንደግፋለን

የኢትዮጵያ መመህራንን ታሪካዊ የትግል ታሪክ ጠንቅቀን እንረዳለን ። ባለፉት የወያኔ ድቅድቅ የጨለማ ዘመን ፥የበደሉ እንፋሎት ከለበለባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች፥ መምህሩ በግንባር-ቀደም ይጠቀሳል።

እነሆ ዛሬ መምህሩ ታሪካዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ልናተኩርበትና ከጎኑ ልንቆም ይገባል ብሎ ኢወክንድ ያምናል ።

የመምህራኑ የሥራ ማቆም አድማ በሌላው ኅብረተስብ ካልታጀበ በቀላሉ ለበቀል ርምጃ እንደሚዳረግ የታወቀ ነው ።

ስለዚህ ኢወክንድ ፥ ለኢትዮጵያ ተማሪዎች በሙሉ ፥ እንዲሁም በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ለሚገኙ የኢወክንድ አባላትና ደጋፊዎቹ ጭምር የመምኅራኑን የአመፅ ትግል በሙሉ ልብ እንድትደገፉ ሀገራዊ ጥሪዎን ያስተላልፋል። የመምኅራኑን አድማ መቀላቀል ወያኔን ለማስወገድ በሚደረገው ብሄራዊ ትግል ወሳኝነት ይኖረዋል ። በተለየ በሀገር ውስጥ የምትገኙ የኢትዮጵያ ተማሪዎች፥ የመምህራኑን አድማ በአስቸኳይ ለመቀላቀል ሀገራዊና ታሪካዊ ኃላፊነት እንዳለባችሁ ጥሪያችንን እናስተጋባለን ።

በውጭ የምንገኝ የኢወክድ አመራርና አባላት ፥ በቅርቡ ለምንጠራው ወያኔን ተቃዋሚ የመምህራን ትግል ደጋፊ የሆነ ፀረ ወያኔ ሰልፍ እንድትጠባበቁ ለሀገር ወዳድ ኃይሎች ጥሪውን ያስተላልፋል ።

ፀረ ኢትዮጵያ የሆነው ወያኔ በታሪካችን ላይ የሚያከናውነውን ጥፋት በመቃወም በተከበሩ ሃይማኖቶች፥ ምዕመናን፥ መቡስሊሙም ሆነ በክርስቲያኑ ላይ የሚፈፀመውን አረመኒያዊ የጥፋት ርምጃ እየተከላከሉ ያሉ ወገኖቻችን መደገፍ ወቅታዊና አንገብጋቢ መሆኑን የሁሉም ዜጋ ግዴታና ኃላፊነት መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም።

ፀረ አማራ የሆኑት የወያኔ መሪዎች ፥ በአማራው ዜጋ ላይ የሚያካሂዱትን ያልተቋረጠ የማፈናቀል የናዜ ፓርቲ አረመኒያዊ ተግባር መወገዝ እንዳለበት ኢወክንድ ጥሪውን ያስተላልፋል።

ኢትዮጵያዊ ዘለዓለማዊ ናት !
የወያኔን ቀብር እናፋጥነው !

EthioLion.Com

Joineprpyl@gmail.com office- 202 291 5832 http://eprpyl.com/
www.facebook.com/eprpyl

Ethiopia Will Prevail!